


ሜይ 2 ቀን 2009 ዓ/ም

# የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በአውስትራሊያ መቋቋሙን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ዘረኛ ቡድን የአፓርታይድ አገዛዝ መውጫና መግቢያ አጥቶ የሰቆቃ ኑሮ በሚገፋበት በዚህ ወሳኝ ወቅት ነጻነት ያለ መስዋትነት እንደማይገኝ የተገነዘቡ ጀግኖች አርበኞች በኢትየዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስር ተደራጅተው፤ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት ክቡር ህይወታቸውን አሳልፈው በመስጠት ግንባሩን ዛሬ ያለበት ደረጃ ላይ በማድረስ ለሕዝባችን ታላቅ የነጻነት ተስፋ ሆነዋል፡፡

ሆኖም ይህን ረዥምና አሰልቺ ጉዞ ሲያደርጉ፤ አቅሙም ሆነ ብቃቱ ካለን ኢትየዮጵያውያኖች በተለይም በተለያዩ የውጭ አገሮች በስደት ላይ ከምንገኘው፤ ጠቀሜታና ቀጣይነት ያለው የሞራል የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ አላደረግንላቸውም፡፡

በመሆኑም የኢትየዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የደረሰበትን የእድገት ደረጃና የሃገራችንን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ተከታታይ የስልክ ስብሰባዎቸን ከኢሕአግ የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ድርጅት ሃላፊ ጋር በማድረግና የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ፤ በመመሪያው መሰረት ለጀግኖች አርበኞች አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ለማድረግ ዛሬ ሜይ 2 ቀን 2009 ዓ/ም የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በአውስትራሊያ ማቋቋማችንን ይፋ ስናደርግ በታላቅ ደስታ ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚ በአውስተራሊ የምትገኙ ኢትዮጵያኖች በሚከተለው ኢማል አድራሻችን
ከኛ ጋር በመገናኘት ለግንባሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ታደርጉ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡
ኢሜል አድራሻችን; eppfAustralia@gmail.com

**አንድነት ኃይል ነው!!**
**የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በአውስትራሊያ**